# የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሕብረት(ኢተፖድኅ)
# ሰክሬታሪያት
# የመጀመሪያ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሕብረት(ኢተፖድኅ) ሰክሬታሪያት) ኦክቶበር 04/1998 በቦን ከተማ(ጀርመን) በመገናኘት የክንውኖችን ሂደት በመገምገም፥ የአጭር ጊዜ የድርጊት ፕሮግራም በመንደፍና፥ ዕቅዶችን በማውጣትና የአሰራር መመሪያ በማውጣት ተካሂዷል።

የስብሰባው ተካፋዮች

1/ዶ/ር ነገደ ጎበዜ የኢተፖድኅ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊ/መንበር
2/ አቶ አረጋዊ በርኼ የኢተፖድኅ አ/ኮ ም/ሊቀመንበር
3/ አቶ ማሞ ይሁኔ የኢተፖድኅ ዋና ጸሐፊ
4/ አቶ ተፈራ ጂሶ  አቶ ኢያሱ ውልደጻድቅን በመወከል በተለዋጭ ተገኝተዋል።

የኢተፖድኅ ሰክሬታሪያት ከተነጋገረባቸውና ውሳኔዎች ያሳለፈባቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ የኢተፖድኅን 1/የኢተፖድኅን መሠረታዊ ሰነድ ስለ ማጽደቅና ቅርንጫፎችና
2/ ደጋፊ ኮሚቴዎችን በአህጉራትና በአገራት ስለማቋቋም፤

ለ/ህብረቱ በተመሠረተ ማግሥት የተከናወኑትን ድርጅታዊ፥ ህብረቱን ለኢትዮጵያውያን ለማስተዋወቅ የተደረጉ ስብሰባ ውጤቶችና ለህብረቱ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ለማስገኘት የተደረጉ የሎቢ ጥረቶችን መገምገምና አጣዳፊ ዕቅዶችን ማውጣት፤

ሐ/ ከሌሎች የተደራጁ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ስብስቦች ጋር ሊኖር ስለሚችለው ግንኙነት፤

መ/የኢተፖድኅ  የፋይናንስና የገንዘብ አቅምን ስለማሳደግ፤

የኢተፖድኅ ሴክሬታሪያት የመነጋገሪያ ርዕሶችን ቅደም ተከተል በመወሰን በቀጥታ ወደ ውይይቱ ከማምራቱ በፊት ለአጭር ሰዓት በወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፥ ኅብረቱ ከተመሠረተ በኋላ ያለውን ህዝባዊ ስሜት፥ በኢህአዴግ በኩል የታዩትን ክስተቶች የፈጠረውን አጠቃላይ መንፈስ የመሳሰሉትን ጉዳዮች በማንሳት ሰፋ ያለ የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ከተደረገ በኋላ በቀጥታ ወደ ተወሰኑት የዕለቱ የመነጋገሪያ ርዕሶች በመግባት ውይይት ተካሂዷል።

ሰክሬታሪያቱ በቅደም ተከተል የተጋገረባቸው ርዕሶች:-

## ሀ/ የኢተፖድኅን 1/መሠረታዊ ሰነድ ስለ ማጽደቅ፥ ቅርንጫፎችና
## 2/ ደጋፊ ኮሚቴዎችን በአህጉራትና በአገራት ስለማቋቋም፤

ሀ.1. የህብረቱን መሠረታዊ ሰነድ ስለ ማጽደቅና የህብረቱን ቅርንጫፎች ስለማቋቋም፥
ኢተፖድኅ የተቀናጀና የህብረቱን ሥራዎች ለመሥራት ይቻለው ዘንድ በ14/09/98 የተሻሻለውን መሠረታዊ ሰነድ የተጠናቀቀ ስለሆነ ለሁሉም አባል ድርጅቶች እንዲላክና በአስተባባሪው ኮሚቴ እንዲጸድቅና በሥራ ላይ እንዲውል ተወስኗል።

ኢተፖድኅ ከተመሠረተ በኋላ ኅብረቱ የቀመላቸውን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ይቻለው ዘንድ የህብረቱን መስራች አባል ድርጅቶች ቅርንጫፎች በሚገኙባቸው አገሮች የኢተፖድኅን ቅርንጫፎች ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ሰክሬታሪያቱ በስፋት ተነጋግሮበታል።
በስብሰባው ላይ የህብረቱን ቅርንጫፎች ለማዋቀር  በመጀመሪያ የህብረቱ አካሎች 1ኛ/ የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ በአስቸኳይ ማቋቋም 2ኛ/ በሰሜን አሜሪካ በማቋቋም በአውሮፓ ደግሞ የህብረቱ ጽ/ቤት

ማዕከል አውሮፓ በመሆኑ ተጨማሪ አህጉራዊ ቅርንጫፍ ማቋቋም አስፈላጊ አለመሆኑን ሰፊ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ለአውሮፓ አንድ አስተባባሪ ከህብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት አቶ ማህሙዳን ለመመደብ በሰብሳቢው ሀሳብ በመቅረቡ ሀሳቡ ድጋፍ ያገኘ ሲሆን አቶ ማህሙዳ የቀረበውን ሀሳብ ከተቀበሉ የአውሮፓ አህጉርን በበላይነት በማስተባበር ሰፊ የሥራ ድርሻ እንደሚኖራቸው ሰክሬታሪያቱ አምኖበታል።
ሰክሬታሪያቱ በዚሁ ርዕስ ላይ ሰፊ ውይይት በማካሄድ የኢተፖድጎ አባል ድርጅቶች ቅርንጫፎቻቸው የኢተፖድጎን የአገር ቅርንጫፎች ለማቋቋም እየተደረገ ባለው ጥረት በቂ ተሳትፎና ትብብር እንዲያደርጉ ለኢተፖድጎ አባል ድርጅቶች መልዕክትና ደብዳቤ እንዲጻፍ ወስኗል።
እያንዳንዱ አገር የኅብረቱን ቅርንጫፎች ካቋቋመ በኋላ የቅርንጫፉን ተጠሪዎች ለኢተፖድጎ ሴክሬታሪያት እንዲያሳውቅ መልዕክት ለቅርንጫፎች እንዲተላለፍም ወስኗል።
በተለይ የህብረቱን ቅርንጫፎች በማደራጀቱ ሂደት የህብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴ አባሎች በሚኖሩባቸው አገሮችና በአጎራባች አገሮች ሀላፊነቱን እራሳቸው በመውሰድ የማደራጀቱን ስራዎች እንዲሰሩ በቀረበው ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኋላ በሚከተለው ሁኔታ የስራ ድልድል ተደርጓል።
1ኛ/ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ በቤልጅዬምና በፈረንሳይ
2ኛ/ አቶ አረጋዊ በርኼ በኔዘርላንድ
3ኛ/ አቶ ተፈራ ጂሶና አቶ ማሞ ይሁኔ በጀርመን
4ኛ/ አቶ ኢያሱ ወ/ጻድቅ በእንግሊዝ
5ኛ/ አቶ አሰፋ ሀብቱ በስዊድንና በኖርዌይ ሀላፊነቱን እንዲወስዱ ስምምነት ተደርሷል።
የህብረቱ ቅርንጫፎች በዋናው የኢተፖድጎ መሠረታዊ ሰነድ ላይ ተመሥርተው የሚከተሉትን የሥራ ድርሻዎች እንዲያከናውኑ ሀሳብ ቀርቧል።
1ኛ/ የኅብረቱን ሰነዶች ማሰራጨት
2ኛ/ ለህብረቱ ዓላማዎች መሳካት በቂ ድጋፍ ለማሰባሰብ ሎቢ ማድረግ፤
3ኛ/ ሰላማዊ ሰልፎችን ሴሚናሮችን የተለያዩ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት መሳተፍ፤
4ኛ/ ለህብረቱ ዓላማዎች መሳካት እርዳታ ማሰባሰብ፥ መላክ፤
5ኛ/ ሌሎች በህብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴና ሰክሬታሪያት የሚሰጡትን ሥራዎችን ማከናወንና
6ኛ/ በአሰራር ተዋረዱ መሠረት ስለ ቅርንጫፉ የህብረት የሥራ እንቅስቃሴን አስመልክቶ ለህብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰክሬታሪያት ሪፖርት ማቅረብን ይጨምራል።

ሀ.2. የህብረቱን የድጋፍ ኮሚቴ ስለማቋቋም፤
የኢተፖድጎ የድጋፍ ምንጩና መሠረቱ የተደራጀበት ኅብረተሰብና ለዓላማው ተግባራዊነት ከጎኑ የተሰለፈውንና የሚሰለፈውን አገር ወዳድና ዲሞክራት ኢትዮጵያውያንን ከትግሉ ጎን በማሰለፍ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማግኘት ሲችል ብቻ ነው ወደ ተነሳለት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መድረስ የሚችለው። በዚህ መሠረት በሙያ፥ በጾታ፥በዕድሜና በነዋሪነት የተደራጁና ያልተደራጁ ኢትዮጵያውያን በድጋፍ ሰጪነት ተደራጅተው በቂ ድጋፍ እንዲሰጡት ለማስቻል በየአገሩ በሚቋቋሙት የህብረቱ ቅርንጫፎች አማካይነት የኢተፖድጎ የድጋፍ ኮሚቴዎች ሁለንተናዊ ጥረት እንዲደረግ ሰክሬታሪያቱ ስምምነት ላይ ደርሷል።
ደጋፊ ኮሚቴዎችን ስለማቋቋምና ደጋፊ ኮሚቴዎች ለህብረቱ የሚሰጡትን ድጋፍና የእርዳታ ሁኔታዎችን አስመልክቶ በሰክሬታሪያቱ አንድ መግለጫና መመሪያ እንዲወጣ ተወስኗል።

## ለ/ህብረቱ በተመሠረተ ማግሥት የተከናወኑትን ድርጅታዊ፥ ህብረቱን ለኢትዮጵያውያን ለማስተዋወቅ የተደረጉ ስብሰባ ውጤቶችና ለህብረቱ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ለማስገኘት የተደረጉ የሎቢ ጥረቶችን መገምገምና አጣዳፊ ዕቅዶችን ማውጣት፤

በዚህ ርዕስ ከፓሪሱ ጉባዔ በኋላ የህብረቱ ዴሊጌሽን ያደረጋቸው የሥራ ጉብኝቶችና ከኢትዮጵያውያን ጋር ያደረጋቸው ግንኙነቶች አስመልክቶ የግምገማ ውይይት ተካሂዷል።
በዚሁ መሠረት የህብረቱ ልዑካን ቡድን በየደረሰባቸው አገሮች የሰጣቸው መግለጫዎችና ኅብረቱን አስመልክተው የሰጧቸው ማብራሪያዎች ጥሩ ውጤትን ያስመዘገቡ ሆነው አግኝቷቸዋል።
ነገር ግን ፕሮግራሞችን በማቀናጀት፥ የህብረቱን የተውጣጣ ልዑክ በመሰየምና ለልዑኩ በህብረቱ አባል ድርጅቶች በቂ ዝግጅትና ድጋፍ እንዲሰጥ ባለመቀነባበሩና እንዲሁም ከኢትዮጵያውያን

የተደረጉ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት በኩል የህብረቱ አባል ድርጅቶች ቅርንጫፎች ለማስተባበር የተደረገው ጥረት የተሚላ አለመሆን ዝግጅቱን በአስተባበረው ወገን ድክመት የታየበትና ለወደፊቱ እነዚህን የመሳሰሉ የቅንብር ጉድለቶች መታረም እንዳለባችው ሀሳብ ቀርቦ በዝግጅቱ ላይ የቀረበውን ሂሳዊ ግምገማም በገንቢ ሂስነት የልዑኩን ጉዞ ያቀናበሩት አስተባባሪ በጸጋ ተቀብለውታል፡፡

በውይይቱ ሂደት ለወደፊትም ህብረቱ በሚያደርጋቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች ሀ/ በጋራ አብሮ የመሥራትን መንፈስ ለማጎልበት ከሀሳብ ማመንጨት ጀምሮ እስከ ውሳኔ አሰጣጥ ድረስ ያሉ ሂደቶች ሁሉንም አባል ድርጅቶች ያሳተፈ እንዲሆን የሚቻለው ጥረት እንዲደረግ ሰክሬታሪያቱ ተስማምቷል፡፡

ከዚሁም ጋር በተያያዘ ኢተፖድን በፓሪሱ ጉባዔ ያጸደቃቸውን ውሳኔዎችና መሠረታዊ ሰነዶች ለማስተዋወቅ የተቀናጀ ጥረት ሰነዶችን ከማስተዋወቅ ጀምሮ በልዑክ እስከ ማስተዋወቁ ድረስ የተቀነባበረ ስራ መሰራት እንደሚያስፈልግ ተወስኗል፡፡

በተለይ የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ ስራ በሰፊው መሠራት እንዳለበት ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን የነጻ ፕሬስን፥ ቀስተደመና ራዲዮና የህብረቱ አባል ድርጅቶች ባላቸው የፕሬስና የራዲዮ ስርጭት የህብረቱን ዓላማዎች በማስተዋወቁ በኩል የጋራ ጥረት እንዲደረግ፤

ኢተፖድን እራሱን ለማስተዋወቅና ውሳኔዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዳው በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ አንድ ዓለም ዓቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ <u>ሰላምና ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ</u> በሚል ከኦክቶበር 29 እስከ ኖቬምበር 7 1998 ድረስ እንዲካሄድ ጥረት እንዲደረግና በኖቬምበር አጋማሽ ላይ በብራሰልስ ከተማ የአውሮፓ ዓቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲደረግ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

የሰላማዊ ሰልፉ መርህ <u>*ሰላምና ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ*</u> የሚል ሲሆን የሰልፉ ዓላማዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፤

1/ የሻዓቢያን ወረራ መቃወም
2/ የብሔራዊ ውይይትን ጥሪ በመደገፍ
3/ የፖለቲካና የኅሊና እስረኞች እንዲፈቱ መጠየቅ
4/ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ መጠይቅ ናቸው፡፡

የሰልፉ አስፈላጊነት ታላቅ ስለሆነና ታላቅ ተጽዕኖም በህወሓት ላይ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ሊያሳድር ስለሚችል የህብረቱ አባል ድርጅቶች አባሎቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን በአጠቃላይ ሌሎችም የተደራጁና ያልተደራጁ ኃይሎችን በማስተባበር እንዲንቀሳቀሱ እንዲደረግና የኢተፖድን አስተባባሪ ኮሚቴ አንድ መግለጫ እንዲያወጣ፤

## ሐ/ ከሌሎች የተደራጁ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ስብስቦች ጋር ሊኖር ስለሚችለው ግንኙነት፤

ኢተፖድን ዓላማውን ለሚቀበሉት የተደራጁ ኃይሎች ክፍት መሆኑ ግልጽ ቢሆንምና ለብሔራዊ ዕርቅ ያቀረበው ጥሪ ለሁሉም መሆኑን ቢረዳም ከዚህ ሌላ በተጓዳኝ እራሳቸውን እያደራጁ ያሉ ውገኖች ከተቻለ ወደ ኅብረቱ የሚመጡበትን ካልተቻለ ደግሞ በጠላትነት ያለመተያየት ሁኔታ እንዲፈጠር ለማስቻል በሰሜን አሜሪካ ከሚገኘው የኢትዮጵያ አገራዊ ጉባዔ ጋር ግንኙነት እንዲፈጠር ለማስቻል በሰክሬታሪያቱ በኩል ደብዳቤ እንዲጻፍና ከደብዳቤውም ጋር የህብረቱ መሰረታዊ ሰነዶች እንዲላኩ ተወሰኗል፡፡

የኢተፖድን አባል ድርጅቶች ሆነው ለአገራዊ ጉባዔ የፈረሙ አባል ድርጅቶች የኢትዮጵያ አገራዊ ጉባዔ ሴኔት መርሆዎች ከኢተፖድን መርሆዎች ጋር መጣጣማቸውን አስመልክተው ማብራሪያ ካላቸው ለህብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲያሳውቁ ደብዳቤ በሁለቱም ቦታ እራሳቸውን ለአደራጁ አባል ድርጅቶች እንዲጻፍ ተወሰኗል፡፡

## መ/የኢተፖድን የፋይናንስና የገንዘብ አቅምን ስለማሳደግና ሌሎች ማሳሰቢያዎች

ኢተፖድን ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የተጠናከረና የቁሳቁስ ድጋፍን ማሰባሰብ እንዳለበት ሰፊ ውይይት ከተካሄደ በኋላ የሚከተሉት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ተወስኗል፡፡

1ኛ/ የህብረቱ አባል ድርጅቶች የአቅማቸውን ያህል እንዲያዋጡ ድብዳቤና መልዕክት ለሁሉም እንዲተላለፍ፤

2ኛ/ የፋይናንስ አቅማቸው ጠንካራ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ እንዲያደርጉ ብደብዳቤ ምጠየቅ፤

3ኛ/ ለኢትዮጵያውያን ማህበሮች ደብዳቤ በመጻፍ የአቅማቸውን እንዲለግሱ መጠየቅና የእርዳታ ማሰባሰቢያ ምሽቶችን እንዲያዘጋጁ መጠየቅ፤

4ኛ/ በሰላማዊ ሰልፎችና ስብሰባዎች እርዳታ መጠየቅ፤
5ኛ/ ከላይ የተጠቀሱትን በተቀናጀ መንገድ ለማስፈም በተለያዩ አገሮች ያሉትን አማጎበራት አድራሻዎች በማሰባሰቡ ብኩል አባል ድርጅቶች እንዲተባበሩ፤
6ኛ/ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንም ትብብርና እርዳታ መጠየቅ፤
6ኛ/ ለህብረቱ ስራዎች መቃናት የፋክስ የኮምፒዩተርና ሌሎች ቁሳቁሶች ማሰባሰብ የሚሉት ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው አበይት ነጥቦች ናቸው።
በመጨረሻም የኢተፖድጎን አድራሻ አስመልክቶ የፖስታ ሳጥንና የኢሜል አድራሻዎችን ለማግኘት በአቶ ማሞ በኩል ጥረት እንዲደረግ በማሰሰብ የዕለቱ ስብሰባ አብቅቷል።

የስብሰባው ሰብሳቢ
ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

የስብሰባው ጸሐፊ
አቶ ማሞ ይሁኔ